የተፈፀመበት የፓርላማ አባላት ምርጫ በአንድ ላይ ከመካሄዱ በፊት፣ መንግሥት ነፃ ጋዜጦችን አግዷል፤ አያሌ የፓርላማ እጩ ተወዳዳሪዎችንም ከምርጫ ውጭ እንዲሆኑ አድርጓል። የምርጫውን መጭበርበር በሰላማዊ መንገድ ለመቃወም በወጡት የፖለቲካ መሪዎች ላይ እና ሁኔታውን ለመዘገብ በስፍራው በተገኙ ጋዜጠኞች ላይ ከመጠን ያለፈ ኃይል ተጠቅሟል፤ በአንዳንድ ሁኔታዎችም ድብደባና እስራት ፈጽሟል። በዚሁ ዓመት፣ መንግሥት በፖለቲካ ጉዳይ ላይ ያተኮሩ ዋና ዋና የተመዘገቡ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ዘግቷል። የተረፉትንም መንግሥታዊ የደህንነት ኃይሎች እያዋከቧቸው ነበር።

ባለፈው ጥቅምት፣ ቦዝኒያና ሄርዘጉቪና የዴይተን ስምምነት ከተፈረመ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ራስ ገዝ የሆነውን የከተማ አስተዳደር መርጧል። ምርጫው ከአለማቀፍ መመዘኛዎች ጋር የሚስማማ ነበር።

በኢንዶኔዢያ ለሦስት ጊዜ በተከታታይ በተደረጉ ምርጫዎች በአያሌ ቁጥር የወጣው መራጭ ሕዝብ የፖለቲካ ሥልጣኑን ይዞ ከነበረው ፕሬዝዳንት ወደተቃዋሚዎች መሪ እንዲሸጋገር በር ከፍቷል። በተጨማሪም ይህ ሂደት ለፓርላማ መቀመጫ የተወዳደሩትን የወታደርና የፖሊስ አባላት እጩዎችን እንዲሸነፉ አድርጓል።

በአፍሪካ ውስጥም ምርጫ ናቸው ሊባሉ በሚችሉ ሂደቶችና በአጠቃላይ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ተካሂዷል በተባለባቸው በጋና እና በሞዛምቢክ ቀደም ሲል በሥልጣን ላይ የነበሩት ፓርቲዎች እንደገና አሸንፈዋል። በአንዳንድ አካባቢዎች መዛባቶች ታይተዋል ቢባልም ሴራሊዮን በ32 ዓመታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የአካባቢ መስተዳድሮችን ምርጫ አካሂዳለች።

በቡሩንዲ የትኩረቱ አቅጣጫ፣ የምርጫ ጊዜውና ወደ ዲሞክራሲ የሚደረገው ሽግግር መዘግየት ትኩረትን ስቧል። የሽግግሩ መንግሥት በአሩሻው የሰላምና የእርቅ ስምምነት መሠረት መካሄድ የነበረባቸውን የአካባቢና ብሔራዊ ምርጫዎች ለማካሄድ ተስኖታል። በአመቱ መጨረሻም፣ በረቂቅ ሕገ መንግሥቱ ላይ ሊሰጥ የሚገባውን ውሳኔ ሕዝብ ላልተወሰነ ጊዜ አስተላልፎታል። የማኦአዊያን አመጽና በኔፓል የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የተፈጠረው መፋጠጥ፣ በዚያ ዓመት ውስጥ ሊካሄድ የነበረውን ምርጫ ከማዘግየቱ ባሻገር የሀገሪቱ ፖለቲካ ይበልጥ እንዲወሳሰብ አስተዋጽኦ አድርጓል።

በሩዋንዳ ቀደም ሲልም ዙሪያቸውን በእሾህ ታጥረው የነበሩ መብቶች፣ ግንባር ቀደም የነበሩት የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅቶች ከተዘጉ በኋላ ወይም በማያጠራጥር መልኩ ከተበታተኑ በኋላ ጨርሶ ጠበዋል። እርምጃው የተወሰደው «መከፋፈልን» ለመዋጋት ተብሎ በተከፈተው ዘመቻ ነው። በመንግሥቱ አንድ ዘገባ መሠረት፣ በዚህ ድርጊት የሚወነጀሉት፣ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋች ቡድኖች፣ ጋዜጠኞች፣ መምህራንና «የዘር ማጥፋት ርእዮተ አለምን» የሚሰብኩ አብያተ ክርስትያን ናቸው።

የኢራን መንግሥት፣ ዜጐቹ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ያላቸውን መብት ለማክበር ያለው ፈቃደኝነት ቁልቁል መውረዱን ቀጥሏል። ፍትሃዊም ነፃም እንዳልነበረ በሰፊው የሚታወቀው 290 መቀመጫዎች ላሉት መጂሊስ (ፓርላማ) የሚካሄደው ምርጫ የካቲት ላይ

ተካሄደ። ወግ አጥባቂው፣ በካህናት የተሞላው የጋርዲያን መማክርት ቀደም ሲል የመጂሊሱ አባላት የነበሩትን ጨምሮ ለውጥ ፈላጊ እጩዎችን በሙሉ ከምርጫው አገለሉአቸው። ለዚህ ማግለል እንደምክንያት ከቀረቡት አንዱ፣ ላለው መንግሥት «በግልጽ የሚታይ ታዛዥነት» የላቸውም የሚል ነበር። እንዲህ በተበላሸ የምርጫ አካሄድ ምክንያትም፣ ለውጥ ፈላጊዎች በፓርላማ ውስጥ እጅግ አነስተኛ መቀመጫ ለመያዝ ተገደዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ ወግ አጥባቂዎቹ በለውጥ ፈላጊዎች ላይ የጀመሩት ጥቃት እንደቀጠለ ነው።

<u>የውስጥና ሌሎች ግጭቶች</u>

የሴራሊዮን የእውነትና የእርቅ ኮሚሽን፣ ግለሰቦች እንደለለባዎች ምሬታቸውን ሊያሰሙ ወይም በጦርነቱ የተካፈሉት በይፋ የሚናዘዙበት ብዛታቸው እስከ 10,000 የሚገመት የተሳተፉበትን ሕዝባዊ የማዳመጥ ሂደት አጠናቋል። ኮሚሽኑም ሕጋዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳዳራዊ የማሻሻያ ሃሣቦችን ወይም ምክሮችን ለመንግሥቱ ሰጥቷል። መንግሥትም በውትድርና ያገለገሉ አያሌ ሕፃናትን ከእስር ፈቷል። በዓመቱ መጨረሻ ላይም በሴራሊዮን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልዑካን ቡድንም ለሴራሊዮን የጦር ኃይልና ለሴራሊዮን ፖሊስ ሀገር አቀፍ ኃላፊነቱን አስረክቧል። ቡድኑ በፀጥታው ምክር ቤት የተሰጠው ኃላፊነት በሚያዝዘው መሠረት በመጪው ሰኔ ወር 1997 ከሴራሊዮን ይወጣል።

የጓቴማላው ፕሬዚዳንት አስካር ቤርገር፣ በ1995 ዓ.ም በተካሄደው የማጣሪያ ምርጫ ከተመረጡ በኋላ፣ የ1988ቱን የሠላም ስምምነት ብሔራዊ አጀንዳ «እንደገና ቀስቅሰው»፣ አገሪቱ ገብታበት በነበረው የእርስ በርስ ጦርነት ወቅት ለደረሰው የሰብአዊ መብቶች ረገጣ በመንግሥት ስም በአርአያነት ይቅርታ ጠየቁ። መንግሥት የወታደራዊ ኃይሉን መጠን ቀነሰ፤ አንዳንድ ዋና ዋና መምሪያዎችንና አሀዶችን በማስወገድ ወታደራዊውን በጀት ቀነሰ። በነሐሴ ወር ላይ የሰብአዊ መብቶችን መጠበቅ አስፈላጊነትን ሳይቀር የሚያካትቱ አንቀጾች ያሉት መርህ አወጣ።

አንድ ዓመት ሙሉ በፈጀው ድርድር፣ በሕዳርና በታህሣሥ ወር ላይ የኮሎምቢያ መንግሥት፣ የተባበሩት የኮሎምቢያ የራስ መከላከያ ኃይሎች ከተባለው ወታደር ቀመስ ኃይል 3,000 የሚገመቱ አባላቱን ሊቀንስ ቻለ። በተጨማሪም፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ የከተሞች ባለሥልጣናት፣ መንግሥት በከተሞቹ ውስጥ ቋሚ የፖሊስ ኃይል ካሰማራ በኋላ ወደየከተሞቻቸው ተመልሰዋል። በዚህም ምክንያት፣ የግድያ፣ የአፈና እና ሌሎች በኃይል የሚፈፀሙ ወንጀሎች ቀንሰዋል።

በሔይቲ፣ ዓመቱን በሙሉ የሀገር ውስጥ ግጭት እንደቀጠለ ነበር። በፖለቲካ ፍጥጫው፣ አሬስቲድን በሚደግፉና በሚቃወሙ አንጃዎች መካከል ከሚፈጠረው አምባጓሮ መናር ጋር ተደምሮ፣ የካቲት 21 ቀን ፕሬዚዳንቱ ሥልጣናቸውን ለቅቀው ወደ ስደት ሲጓዙ ግጭቱ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ ነበር። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሠላም አስከባሪ ኃይል በሀገሪቱ የነበረ ቢሆንም፣ ሕገ መንግሥታዊ በሆነ መንገድ የተቋቋመው የሽግግር መንግሥት ደካማ ነበረ። በመስከረም ወር፣ የአሬስቲድ ደጋፊዎች በፖርቶ ፕሪንስ «አፕሬሽን በግዳድ» በሚል ስያሜ

የብጥብጥና የአመፅ ዘመቻ ጀመሩ። ዘመቻው፣ አፈናን፣ የፖሊስ አባላትንና የሲቪሎችን ራስ መቀላትንና ማቃጠልን፣ ወዳጅ ከጠላት የማይለይ ተኩሶ መግደልን፣ የሕዝብና የግል ንብረቶችን ማውደምንና ማቃጠልን ያጠቃለለ ነበረ። የተቀሰቀሰው አመጽ በፖርቶ ፕሪንስ፣ የትምህርት ቤቶችን፣ የሕዝብ መገበያያ ሥፍራዎችን፣ የወደቡን ሥራና የፍትሕ ሥራውን ለብዙ ሳምንታት አስተጓጉሎት ቆይቷል።

ደቡብ አፍሪካን ተከታታይ ግጭቶች ሲያወኳት ነበሩ። በጃሙ፣ በካሽሚርና በሕንድ ሰሜን ምስራቅ ግዛቶች አመጽ ቀጥሎአል፤ የደህንነት ኃይሎችም የታጠቁ ኃይሎችን ብቻ ሳይሆን ሲቪሎችንም በመግደል ያለአንዳች የተጠያቂነት መንፈስ፣ ሕገወጥ ተግባሮችን ፈጽመዋል። በስሪላንካ፣ መንግሥትም ሆነ አሸባሪው ድርጅት፣ የታሚል ኤላም ሊበሬሽን ታይገር፣ የተኩስ አቁሙን ስምምነት ጥሰዋል። በኔፖል፣ በጥበቃ ስር ያሉ ሰዎች መጥፋት እጅግ አሳሳቢ ችግር ሆኖ ቆይቷል፤ የመንግሥት የደህንነት ኃይሎችም የማኦአዊያን አማጺዎች ደጋፊዎች ናቸው ብለው የሚጠረጥሩአቸውን ግለሰቦች ለማሰርና ይዞ ለማቆየት ሰፊ ሥልጣን እንደተሰጣቸው ነው። እነዚህ ኃይሎች በማን አለብኝነትና በሕገ ወጥነት፣ ገዳይ ኃይል ተጠቅመዋል። የማኦ ተከታዮች አመጽ እንደመቀጠሉ፣ አማጽያን ሲቪሎችን ሲያሰቃዩ፣ የመንግሥት ተወካዮች ደግሞ ሕፃናትን ለውትድርና እየመለመሉ፣ ሠላማዊ ሕዝብን የገደለ የቦምብ ጥቃት አካሂደዋል።

ዲሞክራቲክ ኮንጐን፣ ሩዋንዳን፣ ቡሩንዲንና ዩጋንዳን የሚያጠቃልለው የማእከላዊ አፍሪካ ታላላቅ ኃይቆች አካባቢ ለረዥም ጊዜ፣ በእርስ በርስ ጦርነት፣ እጅግ በሰፋ የዘር ከዘር መጠፋፋት አመፅና በጣም በከፋ የሰብአዊ መብቶች ረገጣ ውስጥ ተዘፍቆ የቆየ ነው። ለአንድ አሠርት እነዚህን ድርጊቶች ሙያ ብለው የያዙት በአካባቢው አገሮች እንደፈለጉ የሚወጡና የሚገቡት የታጠቁ የሚሊሺያ ቡድኖች ናቸው። እነዚህ ቡድኖች ለስልታዊና የተፈጥሮ ሀብቶች እርስበርስ ይወዳደራሉ። የሚኖሩትም ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚለዋወጥ የሕብረትና የመፋረስ አካባቢ ውስጥ ነው። ምሥራቅ ኮንጐን እጅግ አስጊ ከሚያደርጉት ቡድኖች መካከል አንዱ ከ1986ቱ የሩዋንዳ የዘር ማጥፋት ከተፈፀመ በኋላ ከዚያ ፈልሶ በአካባቢው የተጠጋው ቡድን ነው። ይኸው ቡድን ነው በሩዋንዳ ያለውን መንግሥት በመቃወም፤ ድንበር ዘለል ዘመቻ የሚያካሂደው። ይኼው ቡድን በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጐ ውስጥም ሰላማዊ ዜጎችን ይገድላል፤ ሌሎችንም ሕገወጥ ድርጊቶች ይፈጽማል። በአካባቢው የዩጋንዳንና የቡሩንዲን መንግሥታት የሚቃወሙና የሠላም ሂደቱን የሚያደናቅፉ ሌሎች የታጠቁ ኃይሎች እንዳሉ የታወቀ ጉዳይ ነው።

በታላላቆቹ ሀይቆች ለሠላም ያለው እድልና ተስፋ የሚሰጥ ቢሆንም፣ የሰብአዊ መብቶች ረገጣ መደበኛ ተግባር እስኪመስል ይፈፀማል። የዚህ ወንጀል የመጀመሪያ ሰለባዎች ሕፃናት ሲሆኑ፣ በኃይል ለውትድርና ይመለመላሉ፣ ታፍነው ይወሰዳሉ፣ ከዚያም በግዴታ ወታደር ይደረጋሉ። አንዳንድ የአካባቢው መንግሥታት ግን በሠራዊታቸው የሚያገለግሉትን ሕፃናት ወታደሮች ከሠራዊቱ በማሰናበት ረገድ መልካም እርምጃ እያሳዩ ይገኛሉ። አንዳንድ የሚሊሺያ ቡድኖች ብዙኃኑ አባሎቻቸው ሕፃናት ናቸው። አስገድዶ መድፈር፣ ከጊዜ ወደጊዜ የጦርነት ማካሄጃ ዘዴ እየሆነ በመጣ ቁጥር፣ ሴቶችና ልጃገረዶች በተለይ ለአደጋ የተጋለጡ ሆነዋል። አካባቢው፣ በዓለም ከተመዘገቡት 25 ሚሊዮን ተፈናቃዮች መካከል የ5 ሚሊዮን ተፈናቃዮች

መኖሪያ ከመሆኑም በላይ አያሌ ስደኞችንም ያስተናግዳል። ዩናይትድ ስቴትስ፣ በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጐ፣ በዩጋንዳና በሩዋንዳ መካከል ውይይት እንዲካሄድ ጥረት እያደረገች ነው። ትኩረታችንን የታጠቁ ቡድኖች ሊያደርሱ በሚችሉት አደጋ ላይ አድርገን፣ በአካባቢው በሚገኙ አገሮች ውስጥ ያለውን ሁኔታ በቅርበት እንከታተላለን።

በኮትዲቯር፣ በአማጽያኑ ይዞታ ላይ የተፈፀመው ጥቃትና በፈረንሣይ ሰላም ጠባቂ ኃይል ላይ የተወሰደው የአየር ጥቃት በመንግሥትና በአመጽያን መካከል ለ18 ወራት የቆየውን ደካማ የተኩስ አቁም ስምምነት አፈረሰው። ማእቀቦችና የተለያዩ ቅጣቶች እንደሚጣሉበት ቢነገረውም መንግሥት ግጭቱን በወታደራዊ ኃይል ለመፍታት እንደቆረጠ ዝቷል። በአንድ ወቅት፣ በአካባቢው ከሚገኙ አገሮች አንዋ ተብሎ በሚታወቀው ሕግ መሠረት ከዩናይትድ ስቴትስ ጋር ሰፊ የንግድ ግንኙነት ከነበራቸው አገሮች መካከል አንዷ የነበረችው ኮትዲቯር በአሁኑ ዓመት በሀገሪቱ ውስጥ ያለው የደህንነት ሁኔታ አስጊ ስለሆነና የሕግ ልእልናም አስተማማኝ ስላልሆነ ለውጭ ኢንቨስትመንት የማትመችና በአጎዋም ለመጠቀም እንዳትችል ፕሬዚዳንት ቡሽ ወስነዋል።

በሩሲያ ውስጥ፣ በሰሜን ኦሴቲያ ቤስላን በሚገኝ ትምህርት ቤት ላይ የደረሰው ጥቃትና ደህንነት ኃይሎች ተይዘው የነበሩ ሰዎች የደረሱበት አለመታወቅ እየቀጠለ መሄዱ፣ በሰሜን ካውካሰስ እያደር በሚስፋፋው ግጭት መካከል ሁለቱም ወገኖች ለሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ብዙም ግድ እንደሌላቸው ታይቷል። በፖለቲካ ምክንያት የሚደርሱ ተገድዶ መሰወርና ግድያዎችን ጨምሮ ከፍተኛ የመብት ረገጣዎች በመንግሥት ኃይሎችና በቼቺንያ አማፅያን እንደሚፈፀሙ የሚታመኑ ዘገባዎች አሉ። እነዚህን የወንጀል ድርጊቶች ወደሕግ ሊያቀርቡ የሞከሩ ግለሰቦችም የጥቃት ዒላማዎች አድርገዋቸዋል። በሞስኮው የከርሰ ምድር ባቡር ላይ የደረሰው የቦምብ ጥቃት የዚህ ድርጊት አንድ አካል ነበር።

<u>*የሰውነት አንድነት (ዋህድነት)*</u>

ከዓመታት ንትርክ በኋላ፣ የቺሊው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀድሞው የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት አውጉስቶ ፒኖቼን ከሕግ ተጠያቂነት ነፃ የሚያደርጋቸውን ውሳኔ እንዲነሳ ያደረገውን የአንድ ፍርድ ቤት የይግባኝ ውሳኔ አፀና። ታህሣሥ 3 ቀን 1996፣ አንድ ዳኛ አውጉስቶ ፒኖቼ እ.አ.አ በ1970 በ«አፐሬሽ ኮንዶር» በተፈፀሙ ወንጀሎች ተካፋይ ናቸው በማለት ክስ መስርተውባቸዋል።

በማእከላዊ አፍሪካ ሪፐብሊክ፣ ወደ ሕዝባዊ መንግሥት የሚደረገው ሽግግር እንዳለ ሆኖ፣ መንግሥት የደህንነት ምርመራ ክፍሉን በትኖት ነበር። ይህ ክፍል፣ በ1995 ዓ.ም፣ ሰቆቃ መፈጸምን፣ አስገድዶ መድፈርንና ዝርፊያን ጨምሮ በአያሌ የመብት ረገጣዎች የተከሰሰ የወታደራዊ ደህንነት አሀድ ነበር። በ1995 ታህሣሥ ወር ላይ ፕሬዚዳንት ቦዚዜ ስምንት ዓመታት ያህል ታግዶ የቆየውን ቋሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት እንደገና እንዲሰየም አደረጉ። ወታደራዊው ፍርድ ቤት፣ ግድያን፣ አስገድዶ መድፈርንና በመሣሪያ የተደገፈ ዝርፊያን ጨምሮ የተለያዩ የሰብአዊ መብት ረገጣ ክሶችን መርምሯል።

ሰሜን ኮርያ በአለም ከሚገኙ እጅግ ጨቋኝና ጨካኝ መንግሥታት አንዱ እንደሆነ ነው። በግምት ከ150,000 - 200,000 የሚሆኑ የፖለቲካ እስረኞች በሀገሪቱ ውስጥ ራቅ ባሉ ካምፖች ታጉረው ይገኛሉ። አገር ጥለው የሸሹ ሰሜን ኮሪያዊያን እንደሚሉት ከሆነ፣ አያሌ እስረኞች በሚፈፀምባቸው የማሰቃየት ተግባር፣ በረሀብ፣ በበሽታ፣ በመጋለጥ ወይም በሌሎች የተደባለቁ ምክንያቶች ሞተዋል። መንግሥት የዜጎቹን የተለያየ የሕይወት አቅጣጫ በጥብቅ ይቆጣጠራል።

በ19973 ዓ.ም በግብፅ ታውጆ የቆየው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በየካቲት 1995 እንደገና ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ተራዝሟል። ይህ ሕግ ብዙ መሠረታዊ መብቶችን የሚገድብ ነው። የደህንነት ኃይሎች እስረኞችን ማገጣበርና ማሰቃየታቸውን እንደቀጠሉ ናቸው፤ በዚህም ምክንያት ባለፈው ዓመት ብቻ በፖሊስ ጣቢያዎችና በወህኒ ቤቶች አስር ሰዎች እንደተገደሉ ተዘግቧል። ባልታወቀ ምክንያት መታሰርና ተይዞ መቆየት እንዲሁም ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ ለረዥም ጊዜ በእስር መቆየት ጐልተው የሚታዩ ከባድ ችግሮች ናቸው። የወህኒ ቤቶች ይዞታም አስከፊ ነው።

በሶሪያ መንግሥት፣ ተስፋፍቶ በሚካሄደው ሰዎችን የማሰቃየት ተግባር፣ ባለፈው ዓመት ብቻ ቢያንስ ለሰምንት ሰዎች ሞት ምክንያት ሆኗል። ባልታወቀ ምክንያት ማሰር፣ ይዞ ማቆየት፣ ለረዥም ጊዜ ያለፍርድ መታሰር፣ በድህንነት ችሎቶች ቀርበው ኢፍትሃዊ ዳኝነት መቀበል፣ እንዲሁም አስከፊ የወህኒ ቤት ይዞታ ባለፈው ዓመት እንደቀጠሉ ነበሩ። ዓመቱን በሙሉ የደህንነት ኃይሎች፣ በሃሣኬ ግዛት፣ አሌፖ፣ ደማስቆ እና በሌሎች አካባቢዎች ኩርዶችን በጅምላ ሲያስሯቸው ነበር። መጋቢት 3 ቀን 1996 ዓ.ም በሰሜን ምስራቅ ሃሣኬ ግዛት፣ ቃሚሽሊ ውስጥ በአንድ የእግር ኳስ ጨዋታ ላይ በአረቦችና በኩርዶች መካከል በተፈጠረ ሁከት ምክንያት የደህንነት ኃይሎች በሕዝቡ ላይ ተኩስ ከፍተዋል። ከዚያ በተከተሉት ቀኖች በተፈጠረው ረብሻ በደርዘን የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል፤ እስከ 2,000 የሚደርሱ ኩርዶች ታስረዋል፤ እስከ አመቱ መጨረሻ ደግሞ ወደ 300 የሚጠጉ ኩርዶች በእስር እየተንገላቱ፣ በደህንነትና በወታደራዊ ፍርድ ቤቶች ለመቅረብ ቀጠሮ እየጠበቁ ይገኙ ነበር። ለአመታት የት እንደደረሱ ስለማይታወቅ እስረኞች መረጃ ለመስጠት መንግሥት ፈቃደኛ አይደለም።

በኡዝቤኪስታን ውስጥ፣ በወህኒ ቤቶች፣ ከፍርድ ቤት በፊት በማቆያ ሥፍራዎች፣ በፖሊስ ጣቢያዎችና በደህንነት ማጐሪያ ስፍራዎች እስረኞችን ማሰቃየት መደበኛ ተግባር ሆኖ ይቆጠራል። በዚህ ድርጊት ተከሰውና ተረጋግጦባቸው የሚቀጡ እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው። ይሁንና መንግሥት የፖሊስ ተጠያቂነትን ለመመስረትና የማሰቃየት ተግባርን ለመግታት አንዳንድ እርምጃዎችን ወስዷል። በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር በአንዳንድ መምሪያዎች ውስጥ ሰብአዊ መብቶችን የሚረግጡ ሠራተኞችን ሥርአት ለማስያዝ የሚያስችሉ የቅድሚያ የሥነ ሥርዓት መመሪያ አውጥቷል፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እስር ቤቶችን እንዲጐበኙና የወህኒ ቤት ዘበኞችንም በሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ ላይ ሥልጠና እንዲሰጡ ፈቅዷል። በጥበቃ ሥር እንደነበሩ በደረሰባቸው ስቃይ ምክንያት እንደሞቱ በሚነገርላቸው ሰዎች ቅሪተ አካል ላይ፣

አለማቀፍ የፎረንሲክ ምርመራ ባለሙያዎች ምርመራውን እንዲያካሂዱ መንግሥት ፈቃድ ሰጥቷል።

<u>የፕሬስ ነፃነት</u>

በኢራን ውስጥ በዲሞክራሲያዊ መብቶች ጥያቄ ላይ ያነጣጠረው የወግ አጥባቂዎች ጥቃት ከፖለቲካዊ መብቶችም አልፎ ወደሌሎች አካባቢ ተዛምቷል። ለምሳሌ በኢራን ወህኒ ቤት ውስጥ በደረሰበት ጉዳይ ምክንያት ደሙ ወደ አንጐሉ ፈስሶ የሞተውን ኢራናዊ/ካናዳዊ ፎቶግራፍ አንሽ ጉዳይ በ1995 ማጣራቱ ቢጀመርም ባለፈው አመት ላይ ምርመራው ተቋርጧል። መንግሥት ቀስ በቀስ ሁሉንም የአገር ውስጥ ነፃ የብዙኃን መገናኛ ውጤቶችን አፍኖአቸዋል፤ ጋዜጠኞችንም አስሯቸዋል ወይም በፍርሃት ዝም እንዲሉ አድርጓቸዋል። የነፃ ውይይት የመጨረሻ መድረኮች የነበሩት ድረ ገጾችም አሁን በመንግሥት ጫና ስር መውደቅ ጀምረዋል፤ በ1996 እነዚህን ድረ ገጾች የሚከፍቱ ዜጎችን በማሰርና የግዴታ ቃል ሰጥተው እንዲፈርሙ በማድረግ፣ ተጽእኖ እያሳደረባቸው ነው።

በመገናኛ ብዙኃን ላይ እያደር የሚጠነክረው ተጽእኖና ቁጥጥር በሩሲያ ውስጥ ሃሣብን የመግለፅ ነፃነትንና የመገናኛ ብዙኃንን ነፃነት እያዳከመው መጥቷል። በአያሌ የዩሬገርያ ሀገሮች፤ በተለይ በቤላሩስና በአንዳንድ ማእከላዊ የእስያ አገሮች ውስጥ፣ በፕሬስ ላይ የሚደረግ አፈናና ወከባ እየተለመደ የመጣ ተግባር እንደሆነ ተስተውሏል። እንደ ቼቺኒያ ያሉ አስጊ ጉዳዮችን መረጃዎች ማንም በቀላሉ እንዳያገኝ በማሰብ፣ የሩሲያ መንግሥት የመረጠው ብልሀት የብሮድካስት መገናኛ ዘዴ ባለቤትነትን መገደብ ነው። በመንግሥት የሚፈጠረው ተጽእኖም ጋዜጠኞች ራሳቸውን ሳንሱር እንዲያደርጉ ግድ ብሏቸዋል።

በቶጐ፣ መንግሥት ከአውሮፓ ሕብረት ጋር መደበኛ የፖለቲካ ምክክር ካደረገ በኋላ ውጤቱ የተደበላለቀ አዲስ የፕሬስ ሕግ በሥራ ላይ አውሏል። ለብዙ የጋዜጠኛ ጥፋቶች ተብለው ለሚታወቁ ድርጊቶች የእስራት ቅጣትን አስቀርቷል፤ ይሁንና ለአንዳንድ ጥፋቶች - ለምሳሌ አንዳንድ ድርጊቶችን ማነሳሳትን፣ የዘር ጥላቻ መቀስቀስንና በሐሰት ስም መጻፍን ለመሳሰሉ ግን ቅጣቶች አሁንም እንዳሉ ናቸው። ሕጉ ለጋዜጠኞች የባለሙያነት ደረጃም አውጥቷል፤ ስለሆነም ነፃ ጋዜጦች ከጋዜጠኞቻቸው መካከል ሲሶው የሚሆኑት መንግሥት ያወጣውን የደረጃ መለኪያ ማሟላት ይኖርባቸዋል።

በ1994 በተደረገው ዲሞክራሲያዊ ምርጫ፣ ፕሬዚዳንት ቡተፍሊካ ለሁለተኛ ጊዜ ሲመረጡ መንግሥት በመገናኛ ብዙኃን ላይ ተጨማሪ ማገጃዎችን ለመጣል ተንቀሳቅሷል። የስም ማጥፋት ውንጀላና መንግሥት በፕሬስ ላይ የሚያደርገው ማዋከብ በእጅጉ ከፍ አለ። በዚህም አያሌ ጋዜጠኞች ከሁለት እስከ 24 ወራት ታስረዋል፤ ሁለት ጋዜጦች ተዘግተዋል ወይም ታፍነዋል፤ የጋዜጠኞች ራሳቸውን ሳንሱር የማድረግ ዝንባሌአቸውም ተባብሷል።

በቬኔዙዌላ፣ ዓለማቀፍ ድርጅቶችና የአገር ውስጥ ጋዜጠኞች፣ በመገናኛ ብዙኃን ላይ ጥላቻ እንዲነግስ መንግሥት ያበረታታል ሲሉ ይከሳሉ። ባለፈው ታህሳስ ከወጣው አዲስ ሕግ ጋር

ተዳምሮ የሚወሰዱት መንግሥታዊ የአስተዳደር እርምጃዎች፣ በነፃ መገናኛ ብዙኃን ዘዴዎች ላይ አሉታዊ ሕዋ እንዲፈጠር ከማድረጋቸውም በላይ የክስ ማስፈራሪያዎችም ተበራክተዋል።

የኃይማኖት ነፃነት

እነዚህ ጉዳዮች መስከረም 1997 በወጣው ዓለማቀፍ የኃይማኖት ነፃነት ዓመታዊ ዘገባ ላይ በጥልቀት ተወስተዋል፤ እዚህ ዘገባየ ላይ ትኩረት የሚደረገው ዋና ዋና ለውጦችን ወቅታዊ በማድረግ ላይ ይሆናል።

ዓለማቀፉ የኃይማኖት ነፃነት ድንጋጌ፤ በተለይ የኃይማኖት ነፃነትን በብርቱ የሚፃረሩ እና የሚረግጡ አገሮች፣ «በተለይ አሳሳቢ የሆኑ አገሮች» ተብለው እንዲፈረጁ ይጠይቃል። መስከረም 1997 የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፣ በርማን፣ ቻይናን፣ ኢራንን፣ ሰሜን ኮርያን እና ሱዳንን በዚህ መደብ ውስጥ ፈርጀዋቸዋል። ኤሪትሪያ፣ ሳዑዲ አረብያና ቬየትናም ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ መደብ ውስጥ ተፈርጀዋል።

በሳዳም ሁሴን ጊዜ የነበረው በመንግሥት የተደገፈ የኃይማኖት ነፃነት ገፈፋ ከቆመ በኋላ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ከሰኔ 1996 ወዲህ የኢራቅን ስም «በተለይ አሳሳቢ የሆኑ አገሮች» ዝርዝር አስወጥተውታል። በተባበሩት ኃይሎች ኢራቅ ነፃ ከወጣች በኋላ በኃይማኖት ነፃነት ላይ በመንግሥት ምንም ዓይነት እንቅፋት አልተፈጠረም። የኢራቅ የሽግግር አስተዳደር ሕግም «የሃሣብ፣ የሕሊና፣ የኃይማኖት እምነትና የአምልኮ ነፃነት» የተከበረ መሆኑን ይደነግጋል።

የሳዑዲ አረቢያ መንግሥት በኃይማኖት ነፃነት ላይ የሚወስዳቸው እርምጃዎች በእጅጉ የሚያሳዝኑ ናቸው። በ1996 ዓመቱን በሙሉ የዩናይትድ ስቴትስ ባለሥልጣናት ከሳዑዲ ባለሥልጣናት ጋር ኃይማኖታዊ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ወይም የአምልኮ ጉዳዮች ላይ በጥልቀት ሲያወያዩአቸው ቆይተዋል። በ1997 መስከረም ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዓለም አቀፉ ድንጋጌ በሚጠይቀው መሠረት፣ አደገኛ የኃይማኖት ነፃነት አፈና በማካሄዷ ሳዑዲ አረቢያን «በተለይ አሳሳቢ በሆኑ አገሮች» ዝርዝር ውስጥ አስገብተዋታል። መንግሥት ዜጎቹ አንድ ኃይማኖት ብቻ እንዲከተሉ በጥብቅ ያዛል። ዋሀቢ ያልሆኑ የሱኒ ሙስሊሞች፣ የሺአና የሱፊ ሙስሊሞች መገለልና አንዳንድ ጊዜም በማምለክ ሥርዓታቸው ላይ ብርቱ ገደብ ይጣልባቸዋል። የእነዚህ እምነቶች አያሌ መሪዎችም ታስረዋል። መንግሥቱ ማናቸውንም እስላማዊ ያልሆነ ኃይማኖት በአደባባይ የአምልኮ ሥርዓቱ እንዲካሄድ አይፈቅድም። እስላማዊ ያልሆኑ አምላኪዎች፣ የመታገት፣ የእስራት፣ የመሰቃየት ወይም ኦፊሴላዊ ትኩረትን በማስብ የአምልኮ ድርጊት መከሰስና ካገር የመባረር አደጋ ሊያጋጥማቸው ይችላል። ደሞዛቸው በመንግሥት የሚከፈላቸው የመስጊድ ሰባኪዎች በሱኒ ሙስሊሞችና በሌሎች ኃይማኖቶች ላይ ያነጣጠረ አደገኛ ንግግር አያሌ ጊዜ በስብከታቸው ይጠቀማሉ።

ቬየትናም፣ መንግሥት በይፋ ከሚያውቃቸው ኃይማኖቶች ሌላ፣ የኃይማኖት ነፃነትንና የኃይማኖታዊ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ገድባለች። መንግሥት በአስገዳጅ ሁኔታ የራስን እምነት ማወገዝን የሚከለክል ሀገር አቀፍ አዋጅ ለማወጅ ፈቃደኛ አልሆነም፤ በአማኞች ላይ

የሚፈፀመውን አካላዊ ቅጣት አላስቀረም፤ አሁንም ቁጥራቸው የማይናቅ የኃይማኖት እስረኞችን በእስር ቤት እያማቀቀ ነው። በ1993፣ በሀገሪቱ ማእከላዊ ተራራማ አካባቢዎች የተዘጉትን አብያተ ክርስትያን እንዲከፈቱ የፈቀደ ቢሆንም፣ ሌሎች በመቶ የሚቆጠሩትን እንደገና እንዳይከፈቱ ወይም እንዳይመዘገቡ ከልክሏል። ይሁንና «በተለይ አሳሳቢ የሆኑ አገሮች» በሚለው ዝርዝር ውስጥ የሀገሪቱ ስም ከተመዘገበ ወዲህ የኃይማኖት ነፃነትን በማክበር ረገድ የተወሰዱ የማሻሻያ እርምጃዎች አሉ። ባለፈው ህዳር ወር ላይ መንግሥት ኃይማኖትን በተመለከተ ያወጣውን አዲስ ትዕዛዝ አንዳንድ የኃይማኖት መሪዎች አዎንታዊ በሆነ ጥንቃቄ ይመለከቱታል። ባለፈው ታህሣሥ ደግሞ ከ20 ዓመታት ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰሜን ቬዬትናም ወንጌላዊት ቤተክርስትያን ብሔራዊ ጉባኤ አድርጋ አዲስና ነፃ ቦርድ ሰይማለች።

በዚህ ዘገባ ከተዘረዘሩት በኃይማኖት ነፃነት በኩል ከተገኙ ድሎች መካከል አንዱ የአርሜኒያ (የአርመን) የሕዋዊ ምስክሮች ለተከታታይ ዓመታት ማመልከቻቸው ተመላሽ እየሆነባቸው ቆይቶ ባለፈው ጥቅምት ወር መመዝገባቸው ነው። በቦስኒያና ሄርዘጎቪና አዲስ በመንግሥት ደረጃ የተዘጋጀ የኃይማኖት ነፃነት ሕግ በሁለቱም ምክር ቤቶች መጽደቁም ሌላ መልካም እርምጃ ነበረ። ሕጉ፣ ሁሉ አቀፍ የሆነ መብት ለኃይማኖታዊ ማሕበረሰቦች የሚሰጥና ከዚህ በፊት ሕጋዊ እውቅና ላያገኙ የቆዩትንም ይህንኑ የሚያጎናጽፍ ነው። በጆርጂያም በኃይማኖት ሕዳጣን ላይ ይደርስ የነበረው ጥቃት በዚህ ዓመት ቀንሶ ታይቷል።

<u>*የሕዳጣን፣ የሴቶችና የሕፃናት አያያዝ*</u>

ታህሣሥ 20፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዓለማቀፍ ፀረ ሴማዊነት ያዘጋጀውን ዘገባ አጠናቀቀ፤ ከሰኔ 24 ቀን 1995 እስከ ታህሣሥ 5 ቀን 1996 ድረስ ማለት ነው። ከኤምባሲዎቻችን፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ለዚህ ዘገባ ከተላኩልን መረጃዎች በሰፊው በመጠቀም ይህን ዝርዝር ዘገባ ያዘጋጀነው በተለየ የሕግ ድንጋጌ መሠረት ነው።

በቼክና በስሎቫክ ሬፐብሊኮች በሮማዎች ላይ የሚደርሰው መገለል እንደቀጠለ ነው። ሁለቱም መንግሥታት፣ ሕግጋትን በማሻሻል፣ ሮማዎችን የፖሊስ ኃይሎችንና ሕብረተሰቡን የሚያገናኙ በማድረግና በጤና አገልግሎቶች እንዲሰማሩ ጥረት ቢያደርጉም የተጠበቀውን ያህል ውጤት አልተገኘም።

በክሮኤሺያ በያካባቢው የሕዳጣንን መመለስ የሚቃወሙ ቡድኖች ችግር ቢፈጠሩም፤ ለአብዛኞቹ የሰርብ ስደተኞች ንብረታቸው እንዲመለሰላቸው መደረጉ መሻሻል አስገኝቷል። የሕዳጣንን መብት ደካማነት በሚያመለክት ሁኔታ፣ ባለፈው መጋቢት፣ ሁለት ቀን በፈጀው ረብሻ፣ የኮሶቮ ሕዳጣን ሰርቦችና ሌሎች ሕዳጣኖች በኮሶቮ የጥቃት ሰለባዎች ሆነዋል።

በታይላንድ፣ በሀገሪቱ ደቡባዊ ክፍል፣ የደህንነት ኃይሎች በተቃዋሚ ሙስሊሞች ላይ የወሰዱት ሕገወጥ እርምጃ የመንግሥቱን የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ሬከርድ አበላሽቶታል። ሚያዚያ 20 ቀን ፣ የፖሊስና የወታደር ኃይሉ አባላት፣ ያላ፣ ፓታኒ እና ኖራቲዋት በተባሉት ግዛቶች ውስጥ የሙስሊም ተገንጣዮችን ጥቃት ለመመከት ባደረጉት ጥረት ከመቶ ሰዎች በላይ

ገድለዋል። ጥቅምት 15 ቀን ደግሞ ሙስሊም እስረኞችን በጦር ሠራዊት የተፋፈጉና የታጨቁ መኪኖች ወደ አንድ ወታደራዊ ካምፕ ሲያጓጉዟቸው 78 እስረኞች በመታፈን ሞተዋል።

በአፍጋሐኒስታንና በኢራቅ፣ ሴቶች በምርጫ ድምፃቸውን በመስጠት፣ መንግሥታዊ የሥልጣን ስፍራዎችን በመያዝና ለምርጫ በእጩነት በመወዳደር ፖለቲካዊ መብታቸውን በማስከበር በኩል ታይቶ የማይታወቅ እርምጃ ተራምደዋል። በትምህርትና በሌሎች ዘርፎችም ሴቶች መሠረታዊ መብቶቻቸውን በማስከበር ረገድ ታላላቅ ድሎች ተጐናጽፈዋል። በፓኪስታን፣ ሴቶች በእስር በሚቆዩበት ጊዜ ይደርስባቸው የነበረውን የመብት ገፈፋ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ልዩ የሴቶች ፖሊስ ጣቢያዎች በሴት የፖሊስ አባላት ተቋቁመዋል። በተጨማሪም የፍልሚያ (ክብርን ለመጠበቅ ሲባል የሚፈፅም) ግድያ በፓኪስታን እንደቀጠለ ሲሆን፣ አዲስ ሕግ ወጥቶ ጥብቅና ከባድ ቅጣቶች በመጣል የወንጀል ድርጊቱን ለመቀነስ ተሞክሯል። ቅዱሳንን በማዋረድና የሁዱድ ትእዛዛትን በመተላለፍ ለሚቀርቡ ክሶች አዳዲስ ሕጎች ተደንግገዋል፤ ሕገወጥ ድርጊቶችን ለመቀነስም አዳዲስ ሥነ ሥርዓቶች ተሰናድተዋል።

በብዙ አገሮች ውስጥ፣ ከሴቶችና ከሕፃናት መብት መረገጥ ጋር ከተያያዙት ዋና ዋና ችግሮች መካከል ሴቶችንና ሕፃናትን የንግድ እቃ የሚደረጉባቸውን ሁኔታዎች መንግሥታት ጨክነው ሊዋጓቸው ባለመቻላቸው ነው።

በበርማ፣ ከተለያዩ የገጠር መንደሮች ሴቶችና ልጃገረዶች እየተጫኑ በካሚዮን ጣቢያዎች፣ በዓሣ ገበያዎች፣ በጠረፍ ከተሞች፣ በማእድንና በወታደራዊ ጣቢያዎች ለሴተኛ አዳሪነት ይሸጣሉ። የበርማ ወንዶች፣ ሴቶችና ሕፃናትም እንደ እቃ ወደ ሌሎች አገሮች ይሸጣሉ። የመንግሥት የተበላሸ የኢኮኖሚ አስተዳደርና የግዳጅ ሥራ ፖሊሲ ሁኔታውን ጨርሶ አባብሶታል።

በተባበሩት አረብ ኤሚሬቶች፣ ሴቶችና ልጃገረዶች የሚያገለግሉት በሴተኛ አዳሪነትና በግርድና ሲሆን ወንድ ልጆች ደግሞ ግመል ጋላቢዎች ይሆናሉ። በቅርብ ጊዜ የተሰራ አንድ ዘጋቢ ፊልም እንደሚያሳየው ከሆነ፣ የእነዚህ ግመል ጋላቢ ልጆች መከራ የሚጀመረው በጣም በለጋ እድሜአቸው ነው፤ ፊልሙ ለአካል ጉዳት ወይም ለሞት የሚዳርጉትን ጨካኝ ሁኔታዎች ያሳያል፤ ያለ በቂ ምግብ የሚሰቃዩትን፣ በአሠሪዎቻቸው የሚደርስባቸውን አካላዊና ወሲባዊ ሰቆቃም ያሳያል። መንግሥት እነዚህን ሕገ ወጥ ድርጊቶች ለማስቀረት ቃል የገባ ሲሆን፣ የተወሰነ ውጤት ያስገኘ እርምጃም ወስዷል።

መንግሥት ቱሪዝምን ለማስፋፋት የሚወስዳቸው እርምጃዎች የወሲብ ቱሪዝምን ለሚያራምዱ ወገኖች አመቺ ሁኔታን ስለሚፈጥርላቸው በኪዩባ እድሜአቸው የማይፈቅድ ሕፃናት ወሲባዊ ብዝበዛ ይፈፀምባቸዋል።

በኢኳቶሪያል ጊኒ የተጀመረው የሞቀ የነዳጅ ዘይት ንግድ አገሪቱን ለሴተኛ አዳሪነት ለሚጓጓዙት ሴቶች መተላለፊያና ማረፊያ ጣቢያ አድርጓታል። ወደ ወሲብ ንግድና ወደ ግዳጅ ሥራ የተጫኑት ሕንዳዊያን ብዛት በሚሊዮኖች ይቆጠራል። ይህም ወደ ሕንድ ለወሲብ ባርነት ከሚጫኑ በሺህዎች ከሚቆጠሩ ኔፖላዊያንና ባንግላዴሻዊያን ጋር ተደምሮ ነው። በሕንድ በሰው

ልጅ መነገድ ትልቅ ችግር ሆኗል፤ አንዳንድ የመንግሥት ባለሥልጣናትም በንግዱ ከመሳተፋቸውም ሌላ መንገዱን ሁሉ አመቻችተዋል። ሕንድ በሰው ልጅ ላይ የሚደረገውን ንግድ ለመግታት የሚውል ሕግ ባይኖራትም፣ በአንዳንድ ግዛቶቿ መልካም እርምጃዎች የታዩ ሲሆን ማእከላዊው መንግሥትም በቅርቡ፣ ይህን ንግድ ለማስቆም የሚያስችል ሕግ ለማውጣትና ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጦ መነሳቱን ገልጿል።

በታንዛኒያ፣ ለአደጋ በቀላሉ በሚጋለጡ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚደርሰው ጥቃትና መገለል እንደቀጠለ ነው። በነሐሴ ወር በግማሽ ራስ ገዝ የሆነችው የዛንዚባር መንግሥት፣ ግብረ ሰዶማዊነትን ሕገወጥ የሚያደርግና ድርጊቱንም በጥብቅ የሚቀጣ መሆኑን በደሴቲቱ ግዛቱ ላይ አወጀ። በታንዛኒያ፣ አራት ሚሊዮን ሴቶችና ልጃገረዶች ተገርዘዋል፤ ይህ የሚሆነው ድርጊቱን በግማሽም ቢሆን የሚከለክል ሕግ እያለ ነው። ፖሊስም ሕጉን ተግባራዊ ለማድረግ አይተጋም። በአሁኑ ጊዜ ድርጊቱን ተሸሽጎ ለመፈፀም ይመች ዘንድ፣ ሴቶች የሚገረዙበት እድሜ በእጅጉ ቀንሷል።

የሠራተኛ መብቶች

በኢራቅ የሠራተኛ መብቶች በተግባር የዋሉበት ዘርፍ የተወሰነ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት በአብዛኛው፣ የኃይል እርምጃዎች፣ ሥራ አጥነት፣ ከነባራዊ ሁኔታው ጋር በሚገባ ያልተዋሀዱ የሠራተኛ ድርጅቶችና ሕግጋት ስላለ ነው። ይህም ሆኖ ባለፈው ዓመት ማብቂያ ላይ በዓለማቀፍ እርዳታ አንዳንድ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። ብራስልስ በሚገኘው ኢንተርናሽናል ኮንፌዴሬሽን ኦቭ ፍሪ ትሬድ ዩኒዬንስ ዘገባ መሠረት፣ የኢራቅ ሠራተኞች ቀደም ሲል የነበረው ሕግ ይከለክል በነበረው በየሥራ ሥፍራቸው መደራጀት መጀመራቸውንና ቀድሞ የገዥው ፓርቲ ተጽእኖ የሰፈነባቸውን የሠራተኛ ሕብረት መዋቅሮች እንደገና ማንቀሳቀስ መጀመራቸውን ሠራተኞች እንዳስታወቁ ገልጿል። ዓለማቀፉ የሥራ ድርጅት፣ አመቱን በሙሉ ለኢራቅ የሠራተኛ ሕጓ ዓለማቀፍ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን፣ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳዮች ሚኒስቴርን አቅም ለመገንባት ሲረዳ፣ የአስቸኳይ ጊዜ ሥራ አፈላላጊ አገልግሎቶችን ሲመሰርት፣ የክሂል ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን ሲሰጥና የልማት መርሀ ግብሮችን በማዘጋጀት እርዳታ ሲለግስ ቆይቷል።

በሚያዚያ ወር፣ በዓለማቀፍ የሠራተኛ ድርጅት መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 26 መሠረት የተቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን ቤላሩስን ጥሰኛታል፤ ጉብኝቱ የተደረገው፣ መንግሥት በአለማቀፉ የሠራተኛ ድርጅት ስምምነቶች እንደተገለፀው፣ የመሰብሰብና የመደራጀት ነፃነት እንዲሁም በጋራ የመደራደር መብቶች ለሠራተኛው ይከበራል የሚለውንና መንግሥት የተቀበለውን ስምምነት ራሱ ጥሷል የሚለውን ክስ ለማጣራት ነበር። በጥቅምት ወር ላይ የወጣው የአጣሪ ኮሚሽኑ ዘገባ መንግሥት በሀገሪቱ ሠራተኛ ማህበር እንቅስቃሴ ውስጥ አላግባብ ጣልቃ መግባቱን ደምድሟል። ኮሚሽኑም ነፃ የሆኑ ማህበራትን እንዲመዘግብ፣ የመሰባሰብ ነፃነትን የሚገድቡና የሚከለክሉ ሕጐችንና አዋጆችን እንዲያርም፣ ነፃ የሠራተኛ ማህበራትን ከፀረ ማህበራት መድሎ እንዲጠበቁና የኮሚሽኑን ውሳኔዎች እንዲያሰራጭ ለመንግሥት ሣጥብ አቅርቧል። ኮሚሽኑ እስከ

መጪው ሰኔ ወር 1997 ድረስ ከቀረቡት የድርጊት ሃሣቦች አብዛኞቹ እንዲተገበሩ ግልፅ አድርጓል።

በፕሬዚዳንት ቡሽ መሪነት፣ ዩናይትድ ስቴትስ ከዴሞክራሲያዊ አጋሮቻችን ጋር በመሆን ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለዲሞክራሲ የቆምን መሆናችንን እናረጋግጣለን። የቆምንበት መርህ፣ በሕዝባቸው ነፃ ፈቃድ የሚተዳደሩ አገሮች፣ ለልማትና ለሁሉም ይበልጥ ሰላማዊ የሆነች ዓለም ለመፍጠር የማእዘን ደንጊያዎች ናቸው የሚል ነው። የዲሞክራሲያዊ ግዴታችን ተግባራዊነት የተመሠረተው በአራማጆቹ ጽናትና ጥልቅ ስሜት ነው። እነዚህ ከዚህ በኋላ የሚነበቡት ሀገራዊ ዘገባዎች፣ የእድገት ማስጋሌ መጠቆሚያዎችና የወደፊቱን ፈተና ለመጋፈጥ መመሪያዎች ይሁኑ።